## 1/ የ 2001 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም

✓ ***በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም*** ፡- ለተገልጋይ የሚሰጡ አገልግሎቶች መጠንና ጥራት ለማሻሻል መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ አሠራር ተግባራዊ በሆነባቸው ሴክተሮች በተቀረፁ የሥራ ሂደቶች ለተመደቡ ባለሙያዎችና ሠራተኞች ሰፊ ሥልጠና ተሰጥቶ ወደተግባራዊ አፈፃፀም ተሸጋግረዋል ፡፡

✓ *በተለያዩ ምክንያቶች ምደባ ሳያገኙ የቀሩ ሠራተኞች* እንደየትምህርት ደረጃቸውና መስካቸው ታይቶ በአማራጭ መፍትሔ አስተግባሪ ግብረ ኃይል ምደባ ተሰጥቷቸዋል ፡፡

✓ ***በሥነ ምግባር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም*** ፡- ለልማትና ለመልካም አስተዳደር መሠረት የሆነውን ተቋማዊና ማህበራዊ ሥነ-ምግባር እውን ለማድረግ ለተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሥልጠና ተሰጥቷል ፡፡ በአጠቃላይ ከተለያዩ የማኅብረሰብ ክፍሎች ለተውጣጡ 405 ሰዎች፣ ለ 209 ወንዶችና ለ196 ሴቶች ሥልጠና ተሰጥቷል ፡፡

✓ ***በወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም*** ፡- ውስን በጀት አብቃቅቶና በቁጠባ ለመጠቀም የሚያስችል ሥርዓት ከመዘርጋት አንፃር ለተሽከርካሪዎች የሚሞላው ነዳጅ በጌጅ ልኬት እንዲሆንና ንባብ የሌለው የነዳጅ ፍጆታ ቆጣሪ እንደቅድመ ሁኔታ መቀመጡ /መታየቱ/ አበረታች ጅምር ነው ፡፡

በሌላ በኩል የመ/ቤቶች የዕቃ ግዥ በዓመት 2 ዙር እንዲሆን ሲደረግ፣ በሌላ በኩል እንደአስፈላጊነቱ መፈፀም መቻሉ አንዱ ጠንካራ ገጽታው ነው ፡፡

✓ ***በሰው ኃይል አስተዳደር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም*** ፡- የመንግሥት ተቋማትን በሰለጠነ የሰው ኃይል ለማሟላት ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው የመጡ *ወ* <u>*190*</u> *ሴ* <u>*22*</u> *ድምር* <u>*212*</u> ባለሙያዎች በተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች ተመድበዋል ፡፡

✓ ***የሲቪል ሰርቫንቱን አቅም ለማጐልበት*** ፡- በኢ. ሲ. ስ. ኮ በተለያዩ የትምህርት መስኮች በመጀመሪያ ዲግሪ እና በሁለተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የሚገኙና እንዲከታተሉ የመግቢያ ፈተና ተፈትነው እየተጠባበቁ ያሉ ፣

- በልማት ሥራ አመራር ወ 8 ሴ 1 በድምሩ 9
- በከተማ ፕላን ወ 4 ሴ 1 በድምሩ 5
- በፐብሊክ ፋ/ማኔጅመንት ወ 7 ሴ 1 በድምሩ 8
- በከተማ ምህንድስና ወ 4 ሴ 1 በድምሩ 5

በአጠቃላይ ድምር 27 ዕጩዎች ናቸው ፡፡

✓ ***<u>በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ በተደረገው የሠራተኞች ድልድል :-</u>***

በአቅም ግንባታ ሴክተር መስፈርቱን አሟልተው በዋና የሥራ ሂደትና በደጋፊ የሥራ ሂደት ምደባ ያገኙ ሠራተኞች *117* ሲሆን ይህም በመቶኛ *54%* ይሆናል ፡፡

✓ ***<u>በዞን ማዕከል፣ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ በተቀረፁ የሥራ ሂደቶች፡-</u>*** *ወ <u>135</u> ሴ <u>59</u> በድምሩ <u>194</u>* ሠራተኞች ምደባ ያገኙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ *ወ <u>7</u> ሴ <u>7</u> ድምር <u>14</u>* ሠራተኞች በአማራጭ መፍትሔ አስተግባሪ ግብረ ኃይል አማካይነት ምደባ ያገኙ ናቸው ፡፡

✓ ከዚህ ጋር ተያይዞ *ወ <u>98</u> ሴ <u>52</u> በድምሩ <u>150</u>* ሠራተኞች ምደባ እንዳላገኙ ተረጋርጧል ፡፡

✓ ***በወረዳ/ከተማ ደረጃ ምደባ ያገኙ ሠራተኞች አጎዛ*** በትክክል ያልተላለፈልን ቢሆንም ምደባ ያላገኙ *ወ <u>414</u> ሴ <u>183</u> ድምር <u>597</u>* መሆኑን ከተላለፈልን መረጃ መረዳት ተችሏል ፡፡

## ***<u>በበላይ ሥራ አመራር ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም</u>***

✓ ልማትንና መልካም አስተዳደርን እውን ለማድረግ የበላይ አመራር ሚና ከፍተኛ ድርሻ ያለው እንደመሆኑ ለውጡን ለመምራት ተነሳሽነቱ እንዲጨምር በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ ጽንሰ ሀሳብ ላይ ለወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ዋና ኃላፊዎችና ምክትል ኃላፊዎች ሰፊ ሥልጠና ተሰጥቷል ፡፡

## ***<u>በፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም</u>***

### ***<u>በምክር ቤት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም</u>***

✓ በመልካም አስተዳደርና በልማት ዘርፍ የተሰሩና የሚሰሩ ሥራዎች በምክር ቤቱ የበላይ አመራር ወቅታዊ ክትትል እየተደረገበት ይገኛል ፡፡ በተለይ በቀበሌ ደረጃ የዕቅድ ዝግጅትና ክንውን ደረጃ በሸንጐ እየተገመገመ ሲሆን በጐ ጅምር ይታይበታል ፡፡

## ***<u>በፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም</u>***

✓ የተቋማቱን የውሣኔ አሰጣጥ ሂደት የተሻለ ከማድረግም ባሻገር የኅብረተሰቡን በራስ የመተማመን መንፈስ ለማጠናከር በዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና በአንዳንድ ወረዳዎች/ከተሞች በችሎት የሚመደቡ ዳኞች ራሳቸውን በማስተዋወቅና ለባለጉዳዮቹም ሰላምታ በመስጠት ውጥረትን የማርገብ ልምድ እያዳበሩ ያሉበት ሁኔታ ይታያል ፡፡

✓ የፍትህ አሰጣጡን ደረጃ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽ ከማድረግ ጋር ተያይዞ ኅብረተሰቡን እስከ ቦታው ድረስ ሄዶ የማገልገል ሁኔታ ከቦታ ወደ ቦታ እየተስፋፋ ያለ በጐ ጅምር ሆኖ ተገኝቷል ፡፡

*ለምሣሌ* :- በአለታ ወንዶ ወረዳ፣ በገርቢቾ ቀበሌ እና በጉርዳማ ቀበሌ ችሎት የማስቻል ሥራ እየተሰራ ይገኛል ።

ከዚህ በተጨማሪ፣ በፍትህ ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ አገልግሎት ሰጪ አካላት ራሳቸውን ከተገልጋይ የሚለዩበትን የደንብ ልብስ /ገዋን/ በመጠቀም ለተገልጋይ የመረጃ ምንጭ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ ።

## *በመልካም አስተዳደር ፖኬጅ*

✓ አብዛኞቹ የገጠር ቀበሌያት የራሳቸው የሆነ ጽ/ቤት ያላቸው ሲሆን በአንዳንድ ቀበሌያት ራዕይ፣ ተልዕኮ ፣ እሴት በማዘጋጀት መልካም ተሞክሮን እያስፋፉ ይገኛሉ።

*ለምሳሌ :- በአለታ ወንዶ ወረዳ የሽኢቻ ቀበሌ*

✓ በሌላ በኩል ደግሞ የመልካም አስተዳደር ፖኬጁን እውን ለማድረግ የሚያስችል አሰራር ከመዘርጋት አንፃር ለሞዴል ቀበሌዎች፣ ለሞዴል አስተዳዳሪዎች፣ ለሞዴል የልማትና ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ ለሞዴል አርሶ አደሮች የማበረታቻ ሽልማት ተሰጥቷል ።

✓ እንዲሁም፣ ከሁለት የገጠር ወረዳዎች በስተቀር በሌሎች ወረዳዎች ለሚገኙ የገጠር ቀበሌ ሥራ አስኪያጆች ሰፊ ሥልጠና ተሰጥቷል ።

✓ በተለይ፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከማስፋፋት አንፃር፣ ስኬታማ የሆኑ ቀበሌያትን፣ መንደሮችንና አርሶ አደሮችን የመለየት ሥራ ትኩረት ተሰጥቶበት የተሰራ ሲሆን በዚሁ የመለየት ሥራ " *ተአምራዊ ስኬት* " የሚያሰኝ ተሞክሮ የተቀመረ ሲሆን፣ **በዳሌ ወረዳ፣ በአጃዋ ቀበሌ፣ በኤዊቻ የልማት መንደር፣ በአርሶ አደር ዘንድ የተገኘው "*ሳይንሳዊ* " ግኝት በክልሉ የአቅም ግንባታ ሴክተር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች** ተጐብኝቷል ። በተጨማሪም ***በሸበዲኖ ወረዳ በሆወልሶ ቀበሌ*** በአቶ አሰፋ ሳልለው ዘንድ ምርጥ ስኬት መገኘቱና ብዙ ተከታዮችን ማፍራት መቻሉ መልካም ጅማሮ እንደሆነ ታይቷል ።

## *በኢኮቴ መሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት*

✓ የወረዳዎችንና የዞን መምሪያዎችን አቅም ለመገንባት ከክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ የተሰጡ 60 እስካነሮችና 10 ኮምፒዩተሮች ለ 18 የዞን መምሪያዎችና ለ 21 ወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች ተከፋፍለዋል ።

✓ የየሴክተሩን ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዕውቀትና ክህሎት ለማጐልበት ፅንሰ - ሀሳባዊና ተግባራዊ ሥልጠናዎች እየተሰጡ ሲሆን በዞን ማዕከል *ወ 46 ሴ 4 በድምሩ 50* ተሿሚዎችና ሠራተኞች በ " Computer Basics" እና በኢንተርኔት አጠቃቀም ላይ ውጤታማ መሆናቸውን በተደረገው ክትትል በተግባር ታይቷል ።

✓ በተጨማሪም በወረዳዎች፣ በተለይ በአለታ ወንዶ፣ በዳራ፣ ወረዳዎች ለ130 ሠልጣኞች የምሥክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል ፡፡

✓ በሽቦ አልባ ስልክ አጠቃቀም በኩል ደገሞ እስካሁን በነበረን መረጃ መሠረት 2250 የኅብረተሰብ ክፍሎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንደሆኑ ታውቋል ፡፡

✓ በ "LAN" አጠቃቀም በኩል፡ በዳሌ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ኮምፒዩተሮች በ "LAN" ተገናኝተዋል ፡፡

✓ በዞን ማዕከል ደግሞ ትምህርት መምሪያና ወጣቶችና ስፖርት መምሪያ ኔትወርክ ተዘርግቶላቸው የመረጃ ፍሰትና ቅብብሎሹን ፈጣንና ቀልጣፋ ሊያደርጉ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ይገኛሉ ፡፡

✓ እንዲሁም በጥገናና ሶፍት ዌሮችን በመጫን በኩል በተለያዩ የዞናችን ሴክተር መ/ቤቶች የተሰሩ ሥራዎች በወቅቱ የገበያ ዋጋ ሲተምኑ ከብር 13,700 በላይ ወጪ አድነዋል ፡፡

## በሥርዓተ-ፆታና በፀረ - ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ ሜይንስትሪሚንግ

✓ ሁሉም የአቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች ለመ/ቤታቸው ሠራተኞች ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ አስከፊነትና ጎጂነት ብሎም መከላከያ መንገዶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይት አካሂደዋል ፡፡

✓ ሁሉም የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ከመደበኛ በጀታቸው ላይ ተጠቂዎችን ለመደጎም የሚሆን 2% በጀት መድበዋል ፡፡

✓ ከሠራተኞቻቸው የወር ደመወዝ ላይ 0.5% እንዲዋጣ ተደርጎአል ፡፡

✓ የተለያዩ ብሮሸሮች ለሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች ተሰራጭተዋል ፡፡

***ለምሣሌ፡-*** " የመንግሥት መ/ቤቶችና ሠራተኞች የሥራ ቦታዎች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ "

✓ የሴቶችን ተሳትፎና በመ/ቤቶች ያለውን ሥርጭት ለመለየት በተሰበሰበው መረጃ ቋሚ የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኛ ሴቶች ቁጥር 2464 በላይ ሲሆን ይህም ሴት - ወንድ ጥምርታው 1፡4 መድረሱ ታውቋል ፡፡

✓ በመ/ቤት ደረጃ Internal Mainstreaming ለማድረግ የሲዳማ ዞን አቅም ግንባታ መምሪያ፣ ከሲዳማ ዞን ጤና መምሪያ ጋር በመተባበር በዓለም የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ ቀን ከሠራተኞች ጋር የአንድ ሙሉ ቀን የጋራ ውይይት አድርጓል ፡፡

# ያጋጠሙ ችግሮች

✓ የየተቋማቱ መሪዎች የሪፎርም ሥራን እንዲመሩ ከተጣለባቸው ኃላፊነት አንፃር

በቂ ትኩረት ሰጥተው አለመምራታቸው ፣

- ✓ የሪፎርም ሥራን በሚመሩ ኃላፊዎች ዘንድ በየጊዜው የሚደረግ መሸጋሸግ ጅምር ሥራዎች ከውጤት ወይም ከስኬት ሳይደርሱ እንዲቆሙ ምክንያት መሆን፣
- ✓ በተለያዩ ተቋማት የሎጂስቲክ አገልግሎት አለመሟላት፣
- ✓ አዳዲስ በተቀረፁ የሥራ ሂደቶች የባለሙያዎች አለመሟላት፣
- ✓ አዳዲስ በተቀረፁ የሥራ ሂደት መደቦች ላይ ተመድበው የሚሰሩ ባለሙያዎች /አስተባባሪዎች/ ከሥራው ጋር የተመጣጠነ ድርጐ ተግባራዊ ስላልተደረገላቸው የሥራ ስሜት አለመጋጋል ፤
- ✓ ወቅታዊ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል በቂ የተሽከርካሪ አገልግሎት አለመኖር ፣

## 2/ ዓላማ

የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም በመገንባት፣ ፈጣንና ቀጣይነት ያለውን ልማት፣ መልካም አስተዳደር በማስፈን የህዳሴውን ግቦች በማሳካት የሕብረተሰቡን አኗኗር የተሻለ ማድረግ ነው፤

## 3/ ቁልፍ፣ ዓበይትና ንዑሳን የትኩረት መስኮች

### 3.1. ቁልፍ የትኩረት መስክ

በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ የተቃኙ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በሰው ኃይል፣ በአደረጃጀትና በአሠራር በማቀናጀት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ፈጣን፣ ቀልጣፋ እና ተአማኒነት ያለውን የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በማስረፅ ተቋማዊ ለውጥ /Organizational Transformation/ እና መልካም አስተዳደርን እውን ማድረግ ፤

### 3.2. ዓበይት የትኩረት መስኮች

3.2.1. በሁሉም የመንግሥት ተቋማት በወጥነት ተዘጋጅቶ ተግባር ላይ እንዲውል በተደረገ የዕቅድ ዝግጅት፣ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት መሠረት የተቋማትን እስትራቴጂካዊ ዕቅድ መከለስና ዓመታዊ ዕቅድን ማዘጋጀት፣

3.2.2. በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችና በመልካም አስተዳደር የሚከናወኑ ተግባራትንና የተመዘገቡ ውጤቶችን በመገናኛ ብዙሃን ለኅብረተሰቡ እንዲሰራጩ ማድረግ ፣

3.2.3. በአቅም ግንባታ ሴክተር የበላይ አመራሩ በሥርዓተ ፆታና በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንዲመራ ማድረግ ፣

3.2.4. የየሴክተሩን ኃላፊዎች፣ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች እና ባለሙያዎች የዘመናዊ ቴክኖሎጂ /ICT/ አጠቃቀም ክህሎትና ብቃትን ለማሳደግ ፣ የየተቋማቱን የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች አቅም ለማጐልበት የማሠልጠኛና

የጥገና ማዕከላትን ማቋቋም ፡

## 3.3. ንዑሳን የትኩረት መስኮች

3.3.1 በዕቅድ ክንውናቸው የተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴክተሮችን በመለየት ተቋማዊ የሥራ ውድድር መንፈስ የማነሳሳትን ሥርዓት መዘርጋት፣

4.3.2 ልማትን ከማፋጠንና መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አንፃር ስኬታማ ከሆኑ ሴክተሮች፣ ሞዴል የገጠር ቀበሌያት፣ ሞዴል አርሶ አደሮች ዘንድ የልምድ ልውውጥ ማድረግ ፡

3.3.3 ወቅታዊ የግብረ መልስ ሥርዓት መፍጠር ፡

# 4/ የሴክተሩ ግቦች

## 4.1. የቁልፍ የትኩረት መስክ ግቦች

1. መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥን /BPR/ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ያደረጉ 18 የዞን እና 21 የወረዳ ሴክተር መ/ቤቶች፣
2. በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ዲያመንድ መሠረት የሰው ኃይላቸውን 75% እና ከዚያ በላይ ያሟሉ 92 የሥራ ሂደቶች፣
3. ከአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በዕቅድ ክንውን ላይ 4 ዙር የተደረገ ውይይት
4. በ 18 የዞን እና 21 የወረዳ/ከተማ ሴክተር መ/ቤቶች የተዘረጋ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ አዘገጃጀትና አሠራር፣
5. በለውጥ ሥራ አመራር፣ በትግበራ ክህሎት እና በመሪነት ፅንሰ ሀሳብ ላይ ሥርነቀል ሥልጠና ያገኙና አቅማቸው የጐለበተ 31 የዞን እና 751 የወረዳ/ከተማ የበላይ አመራር አካላት፣
6. በሚዛናዊ ውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ ላይ ሥልጠና ያገኙ 2024 የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችና 485 የበላይ አመራር
7. የየተቋማቱን የዕቅድ አፈፃፀምና የፍትህ አፈፃፀም በመከታተልና በመደገፍ ወቅታዊ ግብረ መልስ ለመስጠት የተደረጉ 12 የስቲሪንግ /Steering/ ኮሜቴና 24 የቴክኒክ ኮሚቴዎች ውይይቶች /ስብሰባዎች/ ፡
8. በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ አተገባበር ዙሪያ በወረዳና በዞን ዋና አስተዳዳሪዎች ሰብሳቢነት የተደረጉ 12 ዙር ውይይቶች
9. የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ አተገባበርን ለመከታተልና ለመደገፍ በተቋቋመ ኮሚቴ የተደረገ 24 ዙር ውይይቶች

10.በ19 የገጠር ወረዳና በ524 ቀበሌዎች የመልካም አስተዳደር ፖኬጅን ተግባራዊ ለማድረግ ከማህበረሰብ፣ ከሥራ አስኪያጆችና ከቀበሌ ምክር ቤት ጋር ተቀናጅቶ የተዘረጋ አሠራርና አደረጃጀት፣

11.በ18 የዞን፣ በ21 ወረዳ/ከተማ ሴክተር መ/ቤቶች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ የተቃኘ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አተገባበር ላይ የተደረገ 5ዙር ክትትልና ድጋፍ፣

12.በማስፋፋት እስትራቴጂ ተቀምረው ወደ ሌሎች አቻዎቻቸው እንዲስፋፉ የተደረጉ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ ከየወረዳዎቹ 2 ፣2 የገጠር ቀበሌያት፣ 38 ፣38 መንደሮችና 2 ፣2 አርሶአደሮች ዘንድ የተገኙ የልማትና የመልካም አስተዳደር በጐ ገጽታ ያላቸውን ተሞክሮዎች ስኬቶች፣

13.በ524 ቀበሌያት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ እና አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት ፣

14.በ6 የፍትህ ተቋማት፣ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበርን ተደራሽ፣ ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የተዘረጋ 4 ዙር ድጋፍና ክትትል ፣

15.በዞኑ የተዘረጋና የተስፋፋ የኢ.ኮ.ቴ መሠረተ ልማት 3 የማኀበረሰብ መረጃ ማዕከል የማጠናከር ሥራ 6 /2ዞን፣ 4 በወረዳ/ LAN., 4School Net/

16.100% በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የተደራጀ የመንግሥት ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ፣

17.100% የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈፃፀም ችግሮች፣ ቅሬታዎችና ውሣኔ ያገኙ ጉዳዮች፣

18.በመሥፈርቱ መሠረት ተመልምለው ለትምህርት ዕድል የተላኩ 100% ዕጩዎች

19.በሰው ሀብት ልማትና ሥልጠና አቅማቸው የጐለበተ የዞን፣ የወረዳና ከተማ አስተዳደር 2024 የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችና 6111 ባለሙያዎች፣

20.በሰው ሀብት ሥራ አመራር የሚዘረጉትን ነባርና አዳዲስ የአሰራር ሥርዓቶችን ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ ለ 92 የሂደቱ አስተባባሪዎች የተሰጠ ሥልጠናና 100% የምክር አገልግሎት፣

21. ከተለያዩ ተቋማት ተመርቀው የወጡና ምደባ የተሰጣቸው 100% ምሩቃን

22.በ533 ቀበሌያት የቀበሌ ሥራአስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሠራ የተዘረጋ የአሠራርና የአደረጃጀት ሥርዓት

23.የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን ተግባራዊ ለማድረግ ለ 105 የወረዳ እና ለ5 የዞን ኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን ቡድን የተሰጠ ሥልጠና

## 4.2. ዓበይት የትኩረት መስኮች ግቦች

1. በተቀናጀ የዕቅድ አዘገጃጀት፣ ሪፖርት አቀራረብ/ ሥርዓት ተከልሶ 2 ዙር የተዘጋጀ የሴክተሩ እስትራቴጂካዊ እና የዓመቱ የልማት ዕቅድ፣
2. በመገናኛ ብዙሃን ለተገልጋዩና ለባለድርሻ አካላት 2 ጊዜ የተሰራጩ የሴክተሩ ወቅታዊ መረጃዎች
3. በሴክተሩ የተፈጠረና በተጠናከረ መልኩ የተተገበረ የሥርዓተ ፆታና ፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ እስትራቴጂ ላይ 4 ጊዜ የተደረገ ውይይት
4. የየሴክተሩን ኃላፊዎች፣ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች እና ባለሙያዎች የዘመናዊ ቴክኖሎጂ /ICT/ አጠቃቀም ክህሎትና ብቃትን ለማሳደግ የሚቻልበትን ሥርዓት ለመዘርጋት የተቋቋመ አንድ /1/ የሥልጠናና የጥገና ማዕከል

## 4.3. ንዑሳን የትኩረት መስኮች ግቦች

1. በዕቅድ ክንውናቸው የተሻለ አፈፃፀምን ያስመዘገቡና ከ1ኛ-3ኛ ደረጃ የወጡ፣ ዕውቅና/ማትጊያ/ የተሰጣቸው ሴክተር መ/ቤቶች፣
2. ከሴክተር ወደ ሴክተር፣ ከሞዴል የገጠር ቀበሌ፣ ከሞዴል አርሶ አደሮች ጋር 2 ዙር የተደረገ የልምድ ልውውጥ ፣
3. በዕቅድ ክንውናቸው ተገምግመው ግብረ መልስ የተሰጣቸው 88 የዞን/የወረዳ ሴክተሮች የሥራ ሂደቶች ፣

# 5/ የሴክተሩ ግቦችና የሚጠበቁ ውጤቶች

## 5.1. በቁልፍ የትኩረት መስክ

1. መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥን /BPR/ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ያደረጉ የዞን እና የወረዳ ሴክተር 18 መ/ቤቶች ፣
   - ከመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ አንፃር 100% የተመቻቹ የሥራ ቦታዎች፣
   - ከመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ አንፃር 75% የተሟላ የሰው ኃይል፣
   - ከመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ አንፃር በአገልግሎት አሰጣጥ የረኩ 100% ተገልጋዮች፣
2. በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ዲያመንድ መሠረት የተዘረጋና ተግባር ላይ የዋለ አሰራር ፣
   - የሰው ኃይል 75% እና በላይ የተሟላ የሰው ኃይል፣
   - ለየሥራ ሂደቶቹ የተመቻቸ 75% የሎጂስቲክ አገልግሎት፣

3. በ18 የዞን፣ በ21 የወረዳ/ከተማ ሴክተር መ/ቤቶች የተዘረጋ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ አዘገጃጀትና አሰራር፣
   - BPR ጋር የተቃኘ የሽግግር ጊዜ የሥራ ምዘናና ደረጃ አሰጣጥ ተግባራዊ ያደረጉ ሴክተሮች፣
   - በውጤት ተኮር ላይ የተመሠረተ የማትጊያ ክፍያ የሰጡ ሴክተር መ/ቤቶች፣
   - ከኃላፊነት የሚነሱ ተሿሚዎች ጥቅማ ጥቅም ለማስጠበቅ በተዘረጋ ሥርዓት ጥቅማ ጥቅም ያገኙ ተሿሚዎች ፣
4. ከወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ኃላፊዎች ጋር በዕቅድ አፈፃፀም ላይ 4 ዙር የተደረገ ውይይት
   - በውይይቱ ላይ የተገኙ ኃላፊዎች ብዛት
5. በለውጥ ሥራ አመራር፣ በትግበራ ክህሎት፣ በመሪነት፣ በማስፈፀም አቅም ግንባታ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ … ወዘተ ላይ ሥርነቀልና ተከታታይ ሥልጠና ያገኙና አቅማቸው የጐለበተ የየተቋማቱ የበላይ አመራር የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችና ባለሙያዎች፣
   - የተዘጋጁ 7 የሥልጠና ሰነዶች
   - የተዘጋጁ 100% የሎጂስቲክ አገልግሎቶች
6. በ BSC የውጤት ተኮር ዝግጅትና ምዝና አሠራር ላይ ለበላይ ኃላፊዎችና የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች የተሰጠ ሥልጠና
   - ሥልጠናውን የተካፈሉ ሠልጣኞች ብዛት
7. የየተቋማቱን የዕቅድ አፈፃፀምና የፍትህ አሰጣጥ በመከታተልና በመደገፍ ወቅታዊ ግብረ መልስ ለመስጠት የተደረጉ 12 ዙር የስቲሪንግ /Steering/ ኮሚቴ እና 24 ዙር የቴክኒክ ኮሚቴዎች ውይይቶች /ስብሰባዎች/
   - የየሴክተሩ ስቲሪንግ /Steering/ ኮሚቴዎች 12 ዙር የተደረጉ የግምገማ ውጤቶች
   - በወረዳ/በዞን ደረጃ የተደረጉ 12 ዙር የ “Steering” ኮሚቴ ስብሰባና ውሣኔዎች
8. በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ አተገባበር ዙሪያ በወረዳና በዞን አስተዳዳሪዎች ሰብሳቢነት የተደረጉ ውይይቶች
   - ውይይቱን የተካፈሉ የስቲሪንግ ኮሚቴ አባላት
9. በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ አተገባበር ላይ በወረዳና በዞን ሴክተር መ/ቤቶች ላይ የድጋፍና ክትትል ኮሚቴ 24 ዙር የተደረጉ ስብሰባዎች
   - ውይይቱን/ሰብሰባውን የተካፈሉ ኮሚቴዎች

10. በ19 የገጠር ወረዳና 524 ቀበሌዎች የመልካም አስተዳደር ፖኬጅን ተግባራዊ ለማድረግ ከማኅበረሰብ፣ ከሥራ አስኪያጆችና ከቀበሌ አመራር ጋር ተቀናጅቶ የተዘረጋ አሰራርና አደረጃጀት፣

- የተደራጀና የተዘረጋ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን አሰራር
- የተዘጋጀ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን አሰራር ሥልጠና ሰነድ
- በ524 ቀበሌ በፓኬጅ መሠረት የተቋቋመና ሥራ የጀመረ የኢንስፔክሽን ቡድን
- 4ዙር የተደረገ የኢንስፔክሽን ግብረ መልስ ሪፖርት
- ለቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በኢንስፔክሽን አሰራርና አደረጃጀት ላይ የተሰጠ ሥልጠና፣

11. በ18 የዞንና በ21 ወረዳ/ከተማ ሴክተር መ/ቤቶች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት /BPR/ የተቃኘ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አተገባበር ላይ የተደረገ 5 ዙር ክትትልና ድጋፍ፣

- የተዘጋጁ ቼክ ሊስቶች
- የተሰየመ ግብረ ኃይል /ስድስት ቡድን/
- የተዘጋጀ የክትትልና የድጋፍ ግብረ መልስ ሰነድ /5 የግብረ መልስ ሰነድ/

12. በማስፋፋት እስትራቴጂ ተቀምረው ወደ ሌሎች አቻዎቻቸው እንዲስፋፉ የተደረጉ ስኬቶችና ምርጥ ተሞክሮዎች፣

- የተዘጋጁ 2 የመቀመሪያ ቢጋር /TOR/
- ተቀምረው የተዘጋጁ ከ1ኛ - 3ኛ ደረጃ የወጡ የሴክተሮች ቀበሌዎችና መንደሮች እንዲሁም አርሶ አደሮች ስኬቶች፣
- የተዘጋጁ የምርጥ ተሞክሮ ሰነዶች፣
- በፖኬጁ መሥፈርት መሠረት በሞዴልነት የተመረጡ 3 ግንባር ቀደም አርሶ አደሮች፣
- የተመረጡ ሞዴል 3 መንደሮችና ቀበሌዎች፣

13. በ524 ቀበሌያት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ እና አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት፣

- በ524 ቀበሌዎች የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ እንዲጠናከር የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ አሰራር፣

14. በስድስት የፍትህ ተቋማት፣ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበርን ተደራሽ፣ ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የተዘረጋ 4 ዙር የድጋፍና ክትትል፣

- የተዘጋጁ 19 የተዘዋዋሪ ችሎት ማስቻያ ቦታዎች፣

- ♦ የፍትህ ሂደቶችን ለማቀላጠፍ የተመቻቹ 524 ባሕላዊ የሙግት መፍቻ ቀጠናዎች

15. በዞኑ የተዘረጋና የተስፋፋ የኢ.ኮ.ቴ መሠረተ ልማት፣
    - ♦ የተዘጋጁ 3 የማኅበረሰብ መረጃ ማዕከላት፣
    - ♦ የተዘረጋ የወረዳኔት፣
    - ♦ የተሰራ 4 Website
    - ♦ 4 ዙር የተሰጡ ተከታታይ ሥልጠናዎች
16. 100% በዘመናዊ መረጃ አያያዝ የተደራጀ የመንግሥት ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ፣
    - ♦ በሃርድ ኮፒና ሶፍት ኮፒ የተዘጋጀ የሴክተሩ ሠራተኞች መረጃ፣
17. 100% የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈፃፀም ችግሮች፣ ቅሬታዎችና ውሣኔ ያገኙ ጉዳዮች፣
    - ♦ ውሣኔ ያገኙ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች፣
18. በሰው ሀብት ልማትና ሥልጠና አቅማቸው እንዲገነባ በየተቋማቱ የምልመላ መስፈርት መሠረተ ተመልምለው ለትምህርትና ሥልጠና የተላኩ ባለሙያዎች፣
    - ♦ የተመለመሉ ዕጩዎች ብዛት ፣
19. በሰው ሀብት ልማትና ሥልጠና አቅማቸው የጐለበተ የዞን፣ የወረዳ/ከተማ ጽ/ቤት ባለሙያዎችና አስተባባሪዎች
    - ሥልጠናውን የተካፈሉ 2024 አስተባባሪዎችና 6111 ባለሙያዎች
20. በሰው ሀብት ሥራ አመራር የሚዘረጉትን ነባርና አዳዲስ የአሰራር ሥርዓቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የተሰጠ ሥልጠናና የምክር አገልግሎት፣
    - ♦ የተዘጋጁ 2 የሥልጠና ማኑዋሎች
    - ♦ ለ 92 አስተባባሪዎች የተሰጡ ሥልጠናዎች
21. 100% ምደባ የተሰጣቸው ከተለያዩ ተቋማት ተመርቀው የሚመጡ ባለሙያዎች
    - ♦ የተመደቡ ምሩቃን ብዛት
22. በ19 የገጠር ወረዳዎችና በ 524 ቀበሌያት የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን ተግባራዊ ለማድረግና የቀበሌ ሥራአስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሰራ የተዘረጋ የአሰራርና የአደረጃጀት ሥርዓት፣
    - በየተቋማቱ የተዘረጋ የኢንስፔክሽንና የሱፐርቪዥን አሠራር
    - የተዘጋጀ 1 የሥልጠና ሰነድ

- ሥልጠና የተሰጣቸው ሥራአስኪያጆች ብዛት
- ተቋማዊ አሰራር የዘረጉ 524 ቀበሌያት
- 4 ዙር የተደረገ የኢንስፔክሽን ውጤት ግብረ መልስ

ለገጠር ቀበሌያት ሥራ አስኪያጆች የተሰጠ ሥልጠና

- የሠለጠኑ ሥራ አስኪያጆች ብዛት

24.በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ላይ ሥልጠና የተሰጣቸው የዞንና የወረዳ ኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥንና ሱፐርቪዥዝ ቡድን

- ሥልጠናውን የተካፈሉ ቡድን ብዛት

## 5.2 ዓበይት የትኩረት መስኮች ግቦችና ውጤቶች

1. በተቀናጀ የዕቅድ አዘገጃጀት፣ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት ተከልሶ የተዘጋጀ የሴክተሩ እስትራቴጂካዊና የዓመቱ የልማት ዕቅድ፣
    - 2 ዙር ተከልሶ የተዘጋጀ እስትራቴጂካዊ /የረዥም ጊዜ/ ዕቅድ
    - የተዘጋጀ የዓመቱ የልማት ዕቅድ
    - ተዘጋጅቶ የቀረበ የየሩብ በጀት ዓመት 4 የዕቅድ ክንውን ሪፖርት
2. በመገናኛ ብዙሃን ለተገልጋይና ለባለድርሻ አካላት የተሰራጩ የሴክተሩ ወቅታዊ ዘገባዎች፣
    - 2 ጊዜ የተጠናቀሩ መረጃዎች
    - ለሕዝብ ግንኙነት ሥራ 2 ዙር የተሰራጩ የተመረጡ ዘገባዎች
3. በሴክተሩ የተፈጠረና በተጠናከረ መልኩ የተተገበረ የሥርዓተ ፆታና ፀረ ኤች. አይ.ቪ/ኤድስ/ እስትራቴጂ፣
    - የሴቶችን የመሪነትና የውሣኔ ሰጭነት አቅም ለማጐልበት 1 ጊዜ የተሰጠ ሥልጠና
    - በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ መከላከል ላይ 4 ዙር የተሰጠ ምክርና ድጋፍ
4. የየሴክተሩን ኃላፊዎች፣ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች እና ባለሙያዎች የዘመናዊ ቴክኖሎጂ /ICT/ አጠቃቀም ክህሎትና ብቃትን ለማዳበር የሚቻልበትን ሥርዓት በመዘርጋት የተቋቋመ የሥልጠናና የጥገና ማዕከል፣
    - አንድ የተዘጋጀ ማዕከል፣
    - 100% የተዘጋጁ ቁሳቁሶች፣
    - 25 የተዘጋጁ ዴስክቶፕ ኮምፒውተሮች፣
    - የቀረቡ የጥገና መሣሪያዎች (Tool kit) Spare Parts

## 5.3. ንዑሳን የትኩረት መስኮችና ውጤቶች

1. በዕቅድ ክንውናቸው የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ሴክተር መ/ቤቶች
   - ♦ በክንውን ደረጃቸው የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገቡ፣ በዝርዝር የተለዩ 66 ሴክተር መ/ቤቶች በወረዳ/በዞን ደረጃ ከ1ኛ - 3ኛ የወጡ ፣
   - ♦ ዕውቅና፣ ማትጊያ የተሰጣቸው የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገቡ 66 ሴክተሮች፣
2. ልማትን ከማፋጠንና መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አንፃር ስኬታማ የሆኑ ሴክተሮች፣ ሞዴል የገጠር ቀበሌያት፣ መንደሮችና አርሶ አደሮች፣
   - ♦ ለልምድ ልውውጥ የተመረጡ 2 ሴክተሮች/መ/ቤቶች
   - ♦ » » » 4 ሞዴል ቀበሌያት
   - ♦ » » » 4 ሞዴል መንደሮች
   - ♦ » » » 4 ሞዴል አርሶ አደሮች
3. በዕቅድ ክንውንና አፈፃፀም መነሻ የተዘረጋ ግብረ መልስ ሥርዓት
   - ♦ በክንውናቸው ተገምግመው በየወቅቱ ግብረ መልስ የተሰጣቸው የዞን/ወረዳ/ከተማ ሴክተሮች 88 /የሥራ ሂደቶች/

## 6. የዓመታዊ ግቦች ውጤት ፣ ስኬትና ፋይዳ አመልካቾች

| ተ/ቁ | የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች | የውጤት አመልካቾች /out put indicators/ | /o |
|---|---|---|---|
| 1 | ቁልፍ የትኩረት መስክና ግቦች | በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ የተቃኙ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በሰው ኃይል፣ በአደረጃጀትና በአሠራር በማቀናጀት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ፈጣን፣ ቀልጣፋና ተአማኒነት ያለውን የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በማስረጽ ተቋማዊ ለውጥ /organizational Transformation/ እና መልካም አስተዳደርን ዕውን ማድረግ ፤ | |
| 1.1. | መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ያደረጉ 18 የዞን እና የወረዳ ሴክተር መ/ቤቶች | • ከBPR አንፃር 100% የተመቻቹ የሥራ ቦታዎች<br>• ከBPR አንፃር ከ75% በላይ የተሟላ የሰው ኃይል<br>• ከBPR አንፃር በአገልግሎት አሰጣጥ የረኩ100% ተገልጋዮች ብዛት | •<br>•<br>• |
| 1.2. | በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ ዲያመንድ መሠረት የተዘረጋና ተግባር ላይ የዋለ አሠራር | • የተዘረጋ የምዘና፣ ማበረታቻና ክፍያ ሥራአመራር አሠራር | •<br>• |
| 1.3. | በ18 የዞን እና በ 21 ወረዳ/ከተማ ሴክተር መ/ቤቶች የተዘረጋ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ | • በ BPR የተቃኘ የሽግግር ጊዜ የሥራ ምዘናና ደረጃ አሰጣጥ ሥርዓት፣<br>• በየ6ወር የተሞላ የያንዳንዱ ፈፃሚ የዕቅድ አፈፃፀም ውጤት<br>• ከኃላፊነት የሚነሱ ተጂሚዎች ጥቅማ ጥቅም ለማስጠበቅ የተዘረጋ | •<br>• |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | አዘገጃጀትና አሠራር | ሥርዓት | <br><br>• |
| 1.4. | ከወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ኃላፊዎች ጋር በዕቅድ አፈፃፀም ላይ 4 ዙር የተደረገ ውይይት | • በውይይቱ ላይ የተገኙ ኃላፊዎች ብዛት | • |
| 1.5. | በለውጥ አመራር፣ በትግበራ ክህሎት፣ በመሪነት ጽንሰ ሀሳብ፣ በማስፈፀም አቅም ግንባታ፣ በመልካም አስተዳደር ፖኬጅ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ፣… ሠነዶች ላይ ሥርነቀል ተከታታይ ሥልጠና የተሰጣቸው የየተቋማቱ አመራር፣ ሠራተኞችና የገጠር ቀበሌያት ሥራአስኪያጆች | • የተዘጋጁ የሥልጠና ሰነዶች<br>• የተዘጋጁ የሎጂስቲክ አቅርቦቶች<br>• ሥልጠናውን የተካፈሉ ሠልጣኞች ብዛት | •<br><br>• |
| 1.6. | በ BSC የውጤት ተኮር ዝግድትና ምዘና አመራር ላይ ለበላይ ኃላፊዎችና የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች የተሰጠ ሥልጠና | • ሥልጠናውን የተካፈሉ ተሳታፊዎች ብዛት | • |
| 1.7. | የየተቋማቱን የዕቅድ አፈፃፀምና የፍትህ አሰጣጥ በመከታተልና በመደገፍ ወቅታዊ ግብረ መልስ ለመስጠት የተደረጉ 12 ዙር የስቲሪንግ /Steering/ ኮሚቴና 24 ዙር የቴክኒክ ኮሚቴዎች ውይይት /ስብሰባ/ | • የየሴክተሩ ስቲሪንግ ኮሚቴዎች የግምገማ ውጤቶች<br>• በወረዳ/ዞን ደረጃ የተደረጉ የስቲሪንግ ኮሚቴ ስብሰባና ውሣኔ<br>• በቴክኒክ ኮሚቴ ተቀምሮ ለስቲሪንግ ኮሚቴ የቀረበ የግምገማ ውጤት | • |
| 1.8. | በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ አተገበበር ዙሪያ በወረዳና በዞን አስተዳዳሪዎች ሰብሳቢነት የተደረጉ ውይይቶች | • ውይይቱን የተካፈሉ የእስቲሪንግ ኮሜቴ አባላት | • |
| 1.9. | በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ አተገበበር በዞንና በወረዳ ሴክተር መ/ቤቶች የድጋፍና ክትትል ኮሚቴ 24 ዙር የተደረጉ ስብሰባዎች | • ውይይቱን/ስብሰባውን የተካፈሉ ኮሚቴዎች | • |
| 1.10. | በ19 የገጠር ወረዳና በ524 ቀበሌዎች የመልካም አስተዳደር ፖኬጅን ተግባራዊ ለማድረግ | • የተደራጀና የተዘረጋ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን አሠራር<br>• የተዘጋጀ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን አሠራር ሥልጠና ሰነድ<br>• የኢንስፔክሽን ቡድን የተቋቋመባቸው ወረዳዎችና ቀበሌያት | • |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ከማህበረሰብ፣ከሥራ አስኪያጆችና ከቀበሌ አመራር ጋር በመቀናጀት የተዘረጋ አሰራርና አደረጃጀት ፤ | ብዛት<br>• ሥልጠናውን የተሳተፉ ሠልጣኞች ብዛት | •<br>• |
| 1.11. | በ18 የዞንና በ 21 ወረዳ/ከተማ ሴክተር መ/ቤቶች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ የተቃኘ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አተገባበር ላይ የተደረገ 5 ዙር ክትትልና ድጋፍ | • የተዘጋጁ ቼክ ሊስቶች<br>• የተሰየመ ግብረ ኃይል /ስድስት/<br>• ክትትል የተደረገባቸው ሴክተር መ/ቤቶች ብዛት<br>• የወጣ ወጪ | •<br>• |
| | ***የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች*** | ***የውጤት አመልካቾች***<br>*/out put indicators/* | */o* |
| 1.12. | በማስፋፋት እስትራቴጂ ተቀምረው ወደ ሌሎች አቻዎቻቸው እንዲስፋፉ የተደረጉ ስኬቶችና ምርጥ ተሞክሮዎች | • የተዘጋጀ 2 የመቀመሪያ ቢጋር<br>• ተቀምረው የተዘጋጁ ስኬቶች<br>• የተዘጋጁ የምርጥ ተሞክሮ ሰነዶች<br>• የተመረጡ 3 ሞዴል ቀበሌዎች፣ 3 መንደሮች እና 3 አርሶ አደሮች | • |
| 1.13. | በ524 ቀበሌያት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ እና አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት፤ | • በ524 ቀበሌያት የተዘረጋና የተጠናከረ የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ አሠራር ፣<br>• ግንዛቤ ያገኙ የህብረተሰብ አባላት ብዛት | •<br>• |
| 1.14 | በስድስት የፍትህ ተቋማት፣ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበርን ተደራሽ፣ ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የተዘረጋ 4 ዙር የድጋፍና ክትትል ፤ | • የተዘጋጁ 19 የተዘዋዋሪ ችሎት ማካሄጃ ቦታዎች<br>• የፍትህ ሂደቶችን ለማቀላጠፍ የተመቻቹ 524 ባሕላዊ የሙግት መፍቻ ቀጠናዎች | •<br>• |
| 1.15 | በዞኑ የተዘረጋና የተስፋፋ<br>የኢ.ኮ.ቴ መሠረተ ልማት | • የተዘጋጁ የማኀበረሰብ መረጃ ማዕከላት<br>• የተዘረጋ የወረዳኔት<br>• የተሠራ 4 ዌብሳይት<br>• 4 ዙር የተሠጡ ተከታታይ ሥልጠናዎች | • |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | • |
| 1.1 6 | 100% በዘመናዊ መረጃ አያያዝ የተደራጀ የመንግሥት ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ፣ | • በሃርድ ኮፒ የተዘጋጀ የሴክተሩ ሠራተኞች መረጃ<br>• በሶፍት ኮፒ የተዘጋጀ መረጃ | • |
| 1.1 7 | 100% የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈፃፀም ችግሮች፣ ቅሬታዎችና ውሣኔ ያገኙ ጉዳዮች፣ | • ውሣኔ የተሰጣቸው ቅሬታዎችና አቤቱታዎች | • |
| 1.1 8 | በሰው ሀብት ልማትና ሥልጠና አቅማቸው እንዲገነባ ከየተቋማቱ የምልመላ መስፈርት አሟልተው ለትምህርትና ሥልጠና የተላኩ ባለሙያዎች ፣ | • የአጭር ጊዜ ሥልጠና ያገኙ ሠልጣኞች ብዛት<br>• ለሥልጠናው የወጣ ወጪ<br>• ለረዥም ጊዜ ሥልጠና የተመለመሉ ዕጩዎች ብዛት | •<br>•<br>• |
| ***ተ/ቁ*** | ***የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች*** | ***የውጤት አመልካቾች***<br>***/out put indicators/*** | ***/o*** |
| 1.1 9. | በሰው ሀብት ልማት በሥልጠና አቅማቸው የጐለበተ የዞን፣ወረዳ/ከተማ ሰክተር መ/ቤቶች ፈፃሚዎችና አስተባባሪዎች | • ሥልጠናውን የተካፈሉ 2024 አስተባባሪዎችና 6111 ፈፃሚዎች | • |
| 1.2 0. | በሰው ሀብት ሥራ አመራር የሚዘረጉትን ነባርና አዳዲስ የአሠራር ሥርዓቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የተሰጠ ሥልጠናና የምክር አገልግሎት ፣ | • የተዘጋጁ የሥልጠና ማኑዋሎች<br>• የተሰጡ ሥልጠናዎች<br>• ሥልጠናውን የተካፈሉ ሠልጣኞች ብዛት<br>• ለሥልጠናው የወጣ ወጪ | • |
| 1.2 1. | 100% ምደባ የተሰጣቸው ከተለያዩ ተቋማት ተመርቀው የወጡ ዕጩ ሠራተኞች | • ምደባ የተሰጣቸው ምሩቃን ብዛት | • |
| 1.2 2 | በ524 ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሰራ የተዘረጋ የአሠራርና የአደረጃጀት ሥርዓት | • ሥልጠና የተሰጣቸው ሥራ አስኪያጆች ብዛት<br>• ተቋማዊ አሰራር የዘረጉ ቀበሌያት ብዛት | •<br>• |
| 1.2 3. | ለገጠር ቀበሌየት ሥራ አስኪያጆች የተሰጠ ሥልጠና | • ሥልጠና የገኙ ሥራ አስኪያጆች ብዛት | •<br>• |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | |
| 2.4 | የየሴክተሩን ኃላፊዎች፣ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች እና ባለሙያዎች የዘመናዊ ቴክኖሎጂ/ICT/ አጠቃቀም ክህሎትና ብቃትን ለማሳደግ ፣ የየተቋማቱን የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች አቅም ለማጐልበት የማሠልጠኛና የጥገና ማዕከላትን ማቋቋም ፤ | | |
| 2.4.1 | የየሴክተሩን ኃላፊዎች፣ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች እና ባለሙያዎች የዘመናዊ ቴክኖሎጂ/ICT/ አጠቃቀም ክህሎትና ብቃትን ለማዳበር የሚቻልበትን ሥርዓት በመዘርጋት የተቋቋመ የሥልጠናና የጥገና ማዕከል፤ | • 1 የተዘጋጀ ማዕከል<br>• 100% የተዘጋጁ ቁሳቁሶች<br>• 25 የተዘጋጁ ዴስክቶፕ ኮምፒዩተሮች<br>• የተዘጋጁ የጥገና መሣሪያዎች (Tool kit) | •<br>• |
| 3<br>3.1 | *__ንዑሳን የትኩረት መስኮችና ግቦች__*<br>በዕቅድ ክንውናቸው የተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴክተሮችን በመለየት ተቋማዊ የሥራ ውድድር መንፈስ የማነሳሳትን ሥርዓት መዘርጋት ፤ | | |
| 3.1.1 | በዕቅድ ክንውናቸው የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ሴክተር መ/ቤቶች | • በዝርዝር የተለዩ 66 ሴክተር መ/ቤቶች<br>• ዕውቅና፣ ማትጊያ የተሰጣቸው ከ1ኛ-3ኛ ደረጃ ያገኙ ሴክተር መ/ቤቶች | •<br>• |
| 3.2 | ልማትን ከማፋጠንና መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አንፃር ስኬታማ ከሆኑ ሴክተሮች፣ ሞዴል የገጠር ቀበሌያት፣ ሞዴል አርሶ አደሮች ዘንድ የልምድ ልውውጥ ማድረግ | | |
| 3.2.1 | ስኬታማ የሆኑ ሴክተሮች፣ ሞዴል ቀበሌያት፣ መንደሮችና አርሶ አደሮች | • ለልምድ ልውውጥ የተመረጡ 2 ሴክተር መ/ቤቶች<br>• ለልምድ ልውውጥ የተመረጡ 4 ሞዴል ቀበሌያት<br>• ለልምድ ልውውጥ የተመረጡ 4 ሞዴል መንደሮች<br>• ለልምድ ልውውጥ የተመረጡ 4 ሞዴል አርሶአደሮች | •<br>• |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | |
| 3.3 | ወቅታዊ የግብረ መልስ ሥርዓት መፍጠር | | |
| 3.3 .1 | በዕቅድ ክንውንና አፈፃፀም መነሻ የተዘረጋ የግብረ መልስ ሥርዓት | • ወቅታዊ ግብረ መልስ የተሰጣቸው ሴክተሮች 88 የሥራ ሂደቶች | • |

| ተ/ቁ | ቁልፍ የትኩረት መስክ፣ ዓበይትና ንዑሳን የትኩረት መስኮችና ዓመታዊ ግቦች | የሚጠበቁ ውጤቶች | መለኪያ | የዓመቱ ሥራ መጠን | ፈፃሚ አካል | 1ኛ ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ሐምሌ | ነሐሴ | መስከረ |
| 1 | <u>***ቁልፍ የትኩረት መስክ***</u><br>በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ/BPR/ የተቃኙ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን፣በሰው ኃይል፣ በአደረጃጀትና በአሰራር አቀናጅቶ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ፈጣን፣ ቀልጣፋና ተአማኒነት ያለውን የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋት ተቋማዊ ለውጥ (Organizational Trans formation) እና መልካም አስተዳደርን እውን ማድረግ | | | | በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የተቃኙ ሴክተር መ/ቤቶች | | | |
| 1.1 | መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥን(BPR) ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ያደረጉ የዞንና የወረዳ/ከተማ ሴክተር መ/ቤቶች | ♦ ወደ ሙሉ ትግበራ የተሸጋገሩ ሴክተር መ/ቤቶች ብዛት<br>♦ ከመሠረታዊ የሥራ ሂደት አንፃር የሥራ ቦታዎች የተመቻቹላቸው የሥራ ሂደቶች ብዛት | ቁጥር<br><br>% | 38 ሴክተሮች<br><br>100 | » | ✓<br><br>✓ | ✓<br><br>✓ | ✓<br><br>✓ |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.2 | በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ዲያመንድ መሠረት የተዘረጋና ተግባር ላይ የዋለ አሠራር | ♦ 75% እና በላይ የሰው ኃይል በቅጥር የተሟላላቸው የሥራ ሂደቶች ብዛት<br>♦ የሎጂስቲክ አገልግሎት የተሟላላቸው የሥራ ሂደቶች ብዛት | ቁጥር<br><br>% | 92<br><br>100 | በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የተቃኙ ሴክተር መ/ቤቶች<br><br>» | ✓<br><br>✓ | ✓<br><br>✓ | ✓<br><br>✓ | |
| 1.3 | ተግባር ላይ የዋለ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ አዘገጃጀትና አሠራር | ♦ የBSC ምዘና ሥርዓት የተገበሩ መ/ቤቶች ብዛት<br>♦ በውጤት ተኮር ላይ የተመሠረተ የማትጊያ ክፍያ ሥርዓት ተግባራዊ ያደረጉ መ/ቤቶች ብዛት | ቁጥር<br><br>» | 18 የዞን መምሪያዎችና የ21ወረዳ/ከተማ ጽ/ቤቶች<br><br>» | አቅም ግንባታ ሴክተር | | | | |
| 1.4. | ከወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ኃላፊዎች ጋር በዕቅድ አፈፃፀም ላይ በዙር የተደረገ ውይይት | ♦ በውይይቱ ላይ የተገኙ ኃላፊዎች ብዛት | ዙር | 4 | » | | | | ✓ |
| 1.5. | በለውጥ ሥራ አሠራር፣ በትግበራ ክህሎት፣ በመሪዎች ሚና፣ በማስፈፀም አቅም ግንባታ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ…ወዘተ ላይ ሥር ነቀልና ተከታታይ ሥልጠና ያገኙና አቅማቸው የጐለበተ የየተቋማቱ የበላይ አመራር፣ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችና ባለሙያዎች | ♦ የተዘጋጁ የሥልጠና ሰነዶች<br>♦ የተዘጋጁ የሎጂስቲክ አገልግሎቶች | ጥራዝ<br><br>% | 7<br><br>% | አቅም ግንባታ ሴክተር<br><br>» | | ✓<br><br>✓ | | |
| 1.6. | በBSC የውጤት ተኮር ዕቅድ ዝግጅትና ምዘና አሰራር ላይ ለበላይ ኃላፊዎችና የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች የተሰጠ ሥልጠና | ✫ ሥልጠናውን የተካፈሉ ተሳታፊዎች ብዛት /የበላይ ኃላፊዎችና የሂደት አስተባባሪዎች/ | በቁጥር | 485 እና 2024 በቅደም ተከተል | » | ✓ | ✓ | | |
| 1.7 | የየተቋማቱን የዕቅድ አፈፃፀምና የፍትህ አሰጣጥ በመከታተልና በመደገፍ ወቅታዊ ግብረ መልስ ለመስጠት የተደረጉ የስቲሪንግ /Steering/ ኮሚቴና የቴክኒክ ኮሚቴዎች ውይይቶች /ስብሰባዎች/ | ♦ የየሴክተሩ ስቲሪንግ /Steering/ ኮሚቴዎች ያካሄዱት ስብሰባዎች<br>♦ በዞን/ወረዳ ደረጃ የተደረጉ የ"Steering" ኮሚቴ ስብሰባና ውሣኔዎች | ዙር | 24<br><br>12 | | ✓<br><br>✓ | ✓<br><br>✓ | | |
| 1.8. | በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) አተገባበር ዙሪያ በወረዳና በዞን አስተዳዳሪዎች ሰብሳቢነት የተደረጉ ውይይቶች | ♦ ውይይቱን የተካፈሉ የእስቲሪግ ኮሚቴ አባላት | ዙር | 12 | አስተዳደር ጽ/ቤት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.9. | በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) አተገባበር ላይ በዞንና በወረዳ ሴክተር መ/ቤቶች በድጋፍና ክትትል ኮሚቴ የተደረጉ ስብሰባዎች | ♦ ውይይቱን የተካፈሉ የድጋፍና ክትትል ኮሚቴ አባላት | ዙር | 24 | ሴክተሮች | ✓ | ✓ |
| 1.10 | በ19 ገጠር ወረዳና 524 ቀበሌዎች የመልካም አስተዳደር ፖኬጅን ተግባራዊ ለማድረግ ከማኀበረሰብ ከሥራ አስኪያጆችና ከቀበሌ ካቢኔዎች ጋር ተቀናጅቶ የተዘረጋ አሠራርና አደረጃጀት | ♦ የተደራጀ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን ቡድን<br>♦ ለቀበሌ ሥራ አስኪያጆች በኢንስፔክሽን አሰራርና አደረጃጀት ላይ የተሰጠ ሥልጠና<br>♦ የኢንስፔክሽን ውጤት፣ግብረ መልስና ሪፖርት | ጥራዝ<br>»<br> | | አቅም ግንባታ ሴክተር<br>» | | ✓ |
| 1.11 | በ18 የዞንና በ21 ወረዳ/ከተማ ሴክተር መ/ቤቶች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ/BPR/ የተቃኘ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አተገባበር ላይ 5 ዙር የተደረገ ክትትልና ድጋፍ | ♦ የተዘጋጁ ቼክሊስቶች<br>♦ የተሰየመ ግብረ ኃይል<br>♦ የተዘጋጀ የክትትልና የድጋፍ ግብረ መልስ ሰነድ | ቁጥር<br>»<br>» | 5<br>6<br>5 | | | |
| 1.12 | በማስፋፋት እስትራቴጂ ተቀምረው ወደ ሌሎች አቻዎቻቸው እንዲስፋፉ የተደረጉ ስኬቶችና ምርጥ ተሞክሮዎች | ♦ የተዘጋጀ የመቀመሪያ ቢጋር(TOR)<br>♦ ተቀምረው የተዘጋጁ የሴክተሮች፣ቀበሌዎ ች፣መንደሮችና አርሶ አደር ስኬቶች<br>♦ የተዘጋጁ የምርጥ ተሞክሮ ሰነዶች<br>♦ በፖጀኬጁ መስፈርት መሠረት በሞዴልነት የተመረጡ፣ሞዴል ቀበሌዎች፣መንደሮች ና አርሶ አደሮች | ቁጥር<br>»<br>ጥራዝ<br>ቁጥር | 2<br>3<br>2<br>3 | | | ✓<br>✓<br>✓ |
| 1.13 | በ524 ቀበሌያት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግና አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት | ♦ ስለኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ሥልጠና የተሰጣቸው ቀበሌያትና መንደሮች ብዛት<br>♦ ንዑስ ፖሊስ ጣቢያ የተቋቋመባቸው ቀበሌያት ብዛት | %<br>ቁጥር | 100 | ሁሉም ቀበሌያት | | |
| 1.14 | በ6 የፍትህ ተቋማት፣ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበርን ተዳራሽ፣ ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የተዘረጋ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት | ♦ የተቋቋሙ የተዘዋዋሪ ችሎት ማስቻያ ጣቢያዎች ብዛት<br>♦ የፍትህ ሂደቶችን ለማቀላጠፍ የተመቻቹ ባህላዊ | ጣቢያዎ ች<br>ቁጥር | 19<br>524 | አቅም ግንባታ ሴክተርና የፍትህ ተቋማት | ✓<br>✓ | ✓<br>✓ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሙግት መፍቻ ቀጠናዎች ብዛት | | | | | |
| 1.15 | በዞኑ የተዘረጋና የተስፋፋ የኢ.ኮ.ቴ መሠረተ ልማት | ♦ የተዘጋጁ የማኅበረሰብ መረጃ ማዕከላት ብዛት<br>♦ የተሰራ Website ብዛት<br>♦ ተከታታይ ሥልጠናዎችን የተካፈሉና ያጠናቀቁ የሥራ ሂደት ባለሙያዎች ብዛት | ቁጥር<br>ቁጥር<br>ዙር | 3<br>4<br>4 | አቅም ግንባታ | ✓<br>✓<br>✓ | ✓<br>✓<br>✓ |
| 1.16 | 100% በዘመናዊ መረጃ አያያዝ የተደራጀ የመንግሥት ሠራተኞች አጠቃላይ መረጃ | ♦ በሃርድ ኮፒና በሶፍት ኮፒ የተዘጋጀ የሴክተሩ ሠራተኞች መረጃ<br>♦ ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ መረጃቸውን ወቅታዊ /Up date/ ያደረጉ መ/ቤቶች | % | 100 | ሴክተሮች | ✓ | ✓ |
| 1.17 | 100% የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈፃፀም ችግሮች፣ ቅሬታዎችና ውሣኔ ያገኙ ጉዳዮች | ♦ የተቋቋመ የቅሬታ ማስተናገጃ ዩኒት<br>♦ ውሣኔ ያገኙ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች | በቁጥር<br>% | 1<br>100 | ሴክተሮች | ✓ | ✓<br>✓ |
| 1.18 | በቀረበ መስፈርት መሠረት ምልመላ ተደርጐ ለሥልጠና የተላኩ ዕጩዎች | ✫ መስፈርቱን አሟልተው የተመለመሉ ሠራተኞች ብዛት | በቁጥር | | አቅም ግንባታ | ✓ | ✓ |
| 1.19 | በሰው ሀብት ልማትና ሥልጠና አቅማቸው የጐለበተ፣ የዞን፣ ወረዳ/ከተማ ጽ/ቤት የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችና ባለሙያዎች | ♦ በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች የአጭር ጊዜ ሥልጠና ያገኙ ባለሙያዎች፣ አስተባባሪዎችና ኃላፊዎች ብዛት<br>♦ የረዥም ጊዜ ሥልጠና ያገኙ ሠራተኞች ብዛት | ቁጥር<br>ቁጥር | 2024 አስተባባሪ ዎች 6111 ፈፃሚ ዎ ች<br>» | ሴክተሮች | ✓<br>✓ | ✓<br>✓ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.20 | በሰው ሀብት ሥራ አመራር የሚዘረጉትን ነባርና አዳዲስ የአሠራር ሥርዓቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የተሰጠ ሥልጠናና የምክር አገልግሎት | ♦ የተዘጋጁ የሥልጠና ማኑዋሎች<br>♦ ሥልጠናውን የተካፈሉ ተሳታፊዎች ብዛት<br>♦ የምክር አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ብዛት | ጥራዝ<br>ቁጥር<br>% | 2<br>92<br>100 | | ✓ | ✓ |
| 1.21 | ምደባ የተሰጣቸው ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት የተመረቁ ዕጩ ሠራተኞች | ✯ ምደባ ያገኙ ምሩቃን ብዛት | % | 100 | አቅም ግንባታ ሴክተር እና ሌሎች ሴክተሮች | | |
| 1.22. | በ 19 የገጠር ወረዳዎችና በ 524 ቀበሌዎች የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን ተግባራዊ ለማድረግ የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ መዋቅርን ተቋማዊ ጠንካራ መሠረት እንዲኖረው የተዘረጋ የአሰራርና የአደረጃጀት ሥርዓት | ✯ በየተቋማቱ የተዘረጋ የኢንስፔክሽንና የሱፐርቪዥን አሰራር<br>✯ የተዘጋጀ የሥልጠና ሰነድ<br>✯ ሥልጠና የተሰጣቸው ሥራ አስኪያጆች ብዛት | ጥራዝ<br>ቁጥር | 1<br>524 | የአቅም ግንባታ ሴክተር<br>» | ✓ | ✓ |
| 1.23. | ለሞዴልነት የተመረጡ ወረዳዎች ፣ ቀበሌዎች ፣ መንደሮችና አርሶ አደሮች | ✯ የተዘጋጀ የምልመላ መስፈርት<br>✯ የተለዩ ወረዳዎች፣ ቀበሌያት፣ መንደሮችና አርሶ አደሮች ብዛት | ሰነድ<br>ቁጥር | 1<br>6 | አቅም ግንባታ፣ ጤና፣ትምህርት፣አስ ተዳደር ጽ/ቤት | | |
| 1.24. | በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ላይ ለዞንና ለወረዳ ኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን ቡድን የተሰጠ ሥልጠና | ✯ ሥልጠናውን የተካፈሉ ተሳታፊዎች ብዛት | ቁጥር | ከዞን 5 እና ከወረዳ ዎች 105 | አቅም ግንባታ፣ ጤና፣ትምህርት፣አስ ተዳደር ጽ/ቤት | | |
| 2.1. | ***ዓበይት የትኩረት መስኮች***<br>በሁሉም የመንግሥት ተቋማት በወጥነት ተዘጋጅቶ ተግባር ላይ እንዲውል በተደረገ የዕቅድ ዝግጅት፣ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት መሠረት የተቋማትን እስትራቴጂካዊ ዕቅድ መከለስና ዓመታዊ የልማት ዕቅድን ማዘጋጀት | | | | | | |
| 2.1.1 | በተቀናጀ የዕቅድ አዘገጃጀት ፣ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት መሠረት ተከልሶ የተዘጋጀ የሴክተሩ እስትራቴጂካዊ እና | ♦ ዕቅዳቸውን የከለሱ ሴክተር መ/ቤቶች ብዛት<br>♦ የበጀት ዓመቱን የልማት ዕቅድ በወቅቱ ያዘጋጁ ሴ/መ/ቤቶች ብዛት | ቁጥር<br>»<br>» | 18<br>»<br>» | ሴክተሮች<br>»<br>» | ✓<br>✓ | ✓<br>✓ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የዓመቱ የልማት ዕቅድ | ♦ የየሩብ በጀት ዓመት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ያቀረቡ የወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች | | | | | |
| 2.2. | በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችና በመልካም አስተዳደር የሚከናወኑ ተግባራትንና የተመዘገቡ ውጤቶችን በመገናኛ ብዙሃን ለኅብረተሰቡ እንዲሰራጩ ማድረግ | | | | | | |
| 2.2.1 | በመገናኛ ብዙሃን ለተገልጋይና ለባለድርሻ አካላት የተሰራጩ የሴክተሩ ወቅታዊ ዘገባዎች | ♦ የተጠናቀሩ መረጃዎች<br>♦ ለሕዝብ ግንኙነት ሥራ የተመረጡ ዘገባዎች | ዙር | 2 | አቅም ግንባታ | | ✓ |
| 2.3 | በአቅም ግንባታ ሴክተር የበላይ አመራር በሥርዓተ ፆታና በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንዲመራ ማድረግ | | | | | | |
| 2.3.1 | በሴክተሩ የተፈጠረና በተጠናከረ መልኩ የተተገበረ የሥርዓተ ፆታና ፀረ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ እስትራቴጂ | ♦ የሴቶችን የመሪነትና የውሣኔ ሰጭነት አቅም ለማጐልበት የተሰጠ ሥልጠና<br>♦ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ መከላከል ላይ ምክርና ድጋፍ ያገኙ ተጠቃሚዎች/ተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት | ዙር | 1 | | | ✓ |
| 2.4. | የየሴክተሩን ኃላፊዎች፣ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችና ባለሙያዎች የዘመናዊ ቴክኖሎጂ /ICT/ አጠቃቀም ክህሎትና ብቃትን ለማሳደግና የየተቋማቱን የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች አቅም ለማጐልበት የማሠልጠኛና የጥገና ማዕከልን ማቋቋም | | | | | | |
| 2.4.1 | የየሴክተሩን ኃላፊዎች፣የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችና ባለሙያዎች የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ብቃት ለማሳደግ የሚቻልበትን ሥርዓት ለመዘርጋት የተቋቋመ የሥልጠናና የጥገና ማዕከል | ♦ የተዘጋጀ ማዕከል<br>♦ የተዘጋጀ ቁሣቁስ<br>♦ የተዘጋጁ ዴስክቶፕ ኮምፒውተሮች<br>♦ የቀረቡ የጥገና መሣሪያዎች/Tool kit/ | ቁጥር<br>%<br>ቁጥር | 1<br>100<br>25<br>1 | | | ✓ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3<br><br>3.1. | ***ንዑሳን የትኩረት መስኮች***<br><br>በዕቅድ ክንውናቸው የተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴክተሮችን በመለየት ተቋማዊ የሥራ ውድድር መንፈስ የማነሳሳት ሥርዓትን መዘርጋት | | | | | | |
| 3.1.1 | በዕቅድ ክንውናቸው የተሻለ አፈፃፀምን ያስመዘገቡና ዕውቅና/ማትጊያ/ የተሰጣቸው ሴክተር መ/ቤቶች | ♦ በቼክ ሊስት የተገመገመ የዕቅድ አፈፃፀም<br>♦ በአፈፃፀም መሠረት ደረጃ የወጣላቸው ሴክተር መ/ቤቶች<br>♦ የተሰጠ ሽልማት /ማትጊያ/ | ዙር<br><br>ዙር<br><br>ዙር | 4<br><br>2<br><br>1 | አቅም ግንባታ ሴክተር<br>»<br><br>» | | |
| 3.2. | ልማትን ከማፋጠንና መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አንፃር ስኬታማ ከሆኑ ሴክተሮች፣ሞዴል የገጠር ቀበሌያት፣ሞዴል አርሶ አደሮች ዘንድ የልምድ ለውውጥ ማድረግ | | | | | | |
| 3.2.1 | ከሴክተር ወደ ሴክተር፣ከሞዴል የገጠር ቀበለ፣ከሞዴል አርሶ አደሮች ጋር የተደረገ የልምድ ለውውጥ | ♦ ለልምድ ልውውጥ የተመረጡ መ/ቤቶች ፣ቀበሌያት፣አርሶ አደሮች<br>♦ እንዲስፋፉ የተደረጉ ስኬቶች | ቁጥር | | | | |
| 3.3 | ወቅታዊ የግብረ መልስ ሥርዓት መፍጠር፣ | | | | | | |
| 3.3.1 | በዕቅድ ክንውንና አፈፃፀም መነሻ የተዘረጋ የግብረ መልስ ሥርዓት | ♦ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ የተዘጋጁ ቼክ ሊስቶች/ቅፃቅፆች/<br>♦ ግብረ መልስ ለማዘጋጀትና ለመስጠት የተዘጋጁ ቅፃቅፆች | በዓይነት<br><br>ዙር | 4<br><br>4 | የአቅም ግንባታ ሴክተር | | ✓<br><br>✓ |
| 3.3.2 | በክንውናቸው ተገምግመው በየወቅቱ ግብረ መልስ የተሰጣቸው የዞን/ወረዳ/ከተማ ሴክተሮች /የሥራ ሂደቶች/ | ♦ የተሰጠ ግብረ መልስ | ዙር | 4 | | | ✓ |

## *9/ የክትትል ፣ግምገማ ፣ሪፖርትና ግብረ መልስ ሥርዓት*

የሴክተሩን ዕቅድ በተሟላ ሁኔታ ወደ ተግባር ለማሸጋገርና ለግቦች ስኬታማነት በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች ቁርጠኝነትና የሠራተኞች ተነሳሽነት ወሣኝ ሚና እንዳለው አያጠያይቅም፡፡ በመሆኑም አዎንታዊ ታሳቢዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሴክተሩ ዕቅድ በተሟላ መልኩ ዕውን ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ማድረግ አስፈላጊ ነው ፡፡ በዚህ መሠረት የሚከተለው የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተነድፏል ፡፡

## 9.1. የክትትል ሥርዓት

የክትትል ተግባር በቀጣይነት የዕቅዱ አፈፃፀም በምን ያህል መጠን፣ በምን ያህል የጊዜ ፍጥነት፣ በምን ያህል የጥራት ደረጃና በምን ያህል ወጪ ወይም በአጠቃላይ ዕቅዱ ሊተገበርበት በታሰበባቸው መስፈርቶች፣ የውጤትና ስኬት አመልካቶች /Output and out come indicators/ መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ከተገቢው ምንጭ መረጃ የሚሰበሰብበትና የሚተነተንበት ሂደት ነው ፡፡

በተጨማሪም በክትትሉ ሂደት ተለይተው የወጡ ድክመቶችና ጠንካራ ጎኖች በቀጣዩ የዕቅድ ክንውን ወቅት ግብዓት በመሆን ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችልና ግምገማ በሚካሄድበት ወቅትም በመረጃነት የሚያገለግል ነው ፡፡

የክትትል ሥራ በየደረጃው የሚገኙ የበላይ አመራር አካላትና የስቲሪንግ ኮሚቴ አባላትን ባሳተፈ መልኩ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ሊካሄድ ይገባዋል ፡፡ ኮሚቴውም የተጠናከረ ቅንጅት በመፍጠር ወጥነት ባለው ሁኔታ ለግቦቹ መፈፀም ክትትል ሊያደርግ ይገባል ፡፡

### ከዚህ አኳያ የምንከተላቸው የክትትል ሥርዓቶች /ስልቶች/

1. ወቅታዊ ሪፖርቶችና መረጃዎችን በመጠቀም ክትትል ማድረግ፣
2. የሚከናወኑትን የትኩረት መስኮች በየጊዜው ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት መከታተል፣
3. አጠቃላይ ዞናዊ የአቅም ግንባታ ሴክተር የምክክር ጉባዔን በዓመት አራት ጊዜ ማካሄድ፣
4. የዕቅድ አፈፃፀም ክትትል ሲደረግ በውጤት አመልካቾች መሠረት ማድረግ ሲሆኑ፣

በአጠቃላይ ከሚቀርቡ ሪፖርቶችና ከሚሰበሰቡ የተገልጋይና የባለሙያ አስተያየቶች መነሻ የአስተዳደር መድረኮችን በማዘጋጀት መወያየትና በሥራው ሂደት የተከሰቱ ቁልፍ ችግሮችንና መንስኤዎችን በመለየት የመፍትሄ ሀሳቦችን መለየትና ለቀጣዩ ዕቅድ አፈፃፀም ያላቸውን

ጠቀሜታ መወሰንና መመዝገብ ያሻል ፡፡ የዚህ ሂደት ጠቀሜታው ዕቅድ ፈፃሚ የሆነውን አካል አቅም ለቀጣዩ አፈፃፀም መገንባትና ማዘጋጀት ይሆናል ፡፡

## 9.2. የግምገማ ሥርዓት

የግምገማው ሥርዓት ውጤትንና ስኬትን መለካት በሚያስችል የጊዜ ስፋት መከናወን ስላለበት በየሶስት ወር አንድ ጊዜ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ግምገማ በዕቅድ ውስጥ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ በክትትል የተገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድረግ የሚከናወን ተግባር ነው ፡፡ ይህም ዕቅዱን በጊዜ ገደብ ለመሥራት ከታቀደው ምን ያህሉን በምን ያህል ወጪና በምን ዓይነት ጥራት እንደተተገበረ ካጋጠሙት መሰናክሎችና መልካም ገጠመኞች አንፃር የሚገመገምበት ነው ፡፡

በአጠቃላይ የክትትልና የግምገማው ሥርዓት በተከታታይ የሚከናወን ሆኖ የሚመለከታቸውን አካላት በተሟላ ሁኔታ ያሳተፈ፣ የመረጃው አሰባሰብ ከተለያዩ አካላት ተወስዶ የተነፃፀረና በተገቢው ሁኔታ የተጣራ መሆን ይገባዋል ፡፡ በተጨማሪ ክትትሉም ሆነ ግምገማው ሲካሄድ ከተዘረዘሩት የውጤትና ስኬት አመልካቾች /Out Put and out come indicators/ አንፃር መሆን ይኖርበታል፡፡

## 9.3. ሪፖርትና ግብረ መልስ

በዕቅዱ አፈፃፀም ወቅት በሚካሄዱ የክትትልና ግምገማ ሂደቶች መሠረት ወቅታዊና ትክክለኛ ሪፖርት መቅረብ ይኖርበታል ፡፡ ለዚህም በየደረጃው የሚገኙ ፈፃሚ አካላት ለሚመለከታቸው አካላት በወር፣ በሶስት ወር ፣በስድስት ወርና በዓመት ጊዜ ውስጥ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል ፡፡ ሪፖርቱ የደረሳቸው ክፍሎችም ለተካሄደው አፈፃፀም ሪፖርት፣ መረጃና ግብረ መልስ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡